# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
ወርሃዊ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
የአስረአንደኛው ጉባኤ ጥናት ውጤት

## ብሔራዊ ጉዳይ በኢትዮጵያ


የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፡
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN



ቁጥር፡ 1
መስከረም 1964

## የስራ አስኪያጅ ኮሚቴው ሪፖርት

በፕሬዚዳንቱ በጓድ ነገደ ጎበዜ የተደረገ

ውድ ጓዶችና እንግዶች፡

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ ለ11ኛው ጉባኤ ያደረገውን ጥሪ አክብራችሁ እዚህ በመገኘታችሁ በስራ አስኪያጅ ኮሚቴው ስም ደስታየን ስገልጽ እንኳን ደህና መጣችሁ እያልኩ ነው። እንደዚሁም ደግሞ ለዚሁ ጉባኤያችን ከአሜሪካ ድረስ በመምጣት ከመሀከላችን የተገኙትን ጓዶች ስንቀበል ከፍ ያለ ደስታ እየተሰማን ነው። ድጋፋቸውን ለገለጹልን ልዩ ልዩ ድርጅቶችም ለኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ላበረከቱት ጸረኢምፔሪያሊስት አንድነት ከፍ ያለ መስጋናችንን እናቀርባለን።

በዛሬው ወቅት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በአለም በሙሉ ከሚገኙ ጸረኢምፔሪያሊስት ንቅናቄዎች ጋር እየጠበቀ የሚሄድ አንድነት በመመስረት ላይ ነው። የዚሁም አንድነት መሰረቱ በሀገራችን፡ በመላው አፍሪቃ፡ በእስያና በላቲን አሜሪካ የተጠቁ ህዝቦች በሙሉ ከአንድ የጋራ ጠላት ጋር የሚያደርጉት ትግል ነው።

ይህ የአለም ህዝቦች የጋራ ጠላት ኢምፔሪያሊዝም ሲሆን የትግላችን ዋና አላማ ደግሞ እሱንና በየሀገሩ ያስቀመጣቸውን አሽንጉሊቶች ጠራርጎ ጥሎ በፍትህና በህዝባዊ ዴሞክራሲ ላይ የተመሰረተ አዲስ ስርአት ለማቆም ነው።

ከጊዜ ወደጊዜ እየመረረ የሚሄደው የኢምፔሪያሊስቶች ዘረፋ እየዓበረና እየተፋፋመ በሚሄድ የህዝብ አመጽ በመመታት ላይ ነው። የዚህ ትግል እየተፋፋመ መሄድ ዛሬ ለዘመኑ መልክ ከሚሰጡት ታላላቅ ቅራኔዎች አንዱና እንዲያውም ዋናው በያለበት በተነሱት ተበዝባዥ ህዝቦችና በኢምፔሪያሊዝም መሀከል ያለው ቅራኔ መሆኑን በግልጽ ያመለክታል።

እርግጥ ይህ ሁሉ አስቸጋሪ፡አደገኛና አታካች ስራ ነው፡፡ግን ከመሀከላችን ሬቮሉሽን የልጅ ጨዋታ ነው የሚል ያለ አይመስለንም፡፡በየመስመሩ፡በየቀኑ፡በየአጋጣሚው የማይቋረጥ ረዥም ትግልን ይጠይቃል፡፡

በዚህ ቀስ በቀስ በሚመራ ጠምራና የተቀናበረ ፖለቲካ የሚገኘው የጠበቀ አንድነት በጠላቶቻችን ላይ ለምንጎናጸፈው ድልና ለነጻነት ጉዞአችን ትልቅ ዋስትና ነው፡፡ስለዚህም እንደሌሎች መሰረታዊ የህዝብ አላማዎች ያለትግል አይገኝም፡፡

እንደነጻነታችን፡እንደእርምጃችን፡እንደሰብአዊ መብቶቻችን ይህም እርግጠኛ የህዝብ አንድነት በግድ፡በሃይልና በቆራጥ ትግል ከኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች ተነጥቆ በአዲስ መንፈስ የሚመሰረት አንድነት ነው፡፡

ስለዚህ ለዚህ የምናደርገውን ትግል በምንም አይነት ከጠቅላላው ከጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስት ትግላችን ለይተን አናየውም፡፡ለይቶ ለማየትም የሚደረጉትን መከራዎች እንቀጋቸዋለን፡፡

ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይውደሙ

የብሄሮች ነጻነትና እኩልነት ይከበር

የየብሄሮች ሰፊ ህዝቦች አንድነት ይስፈን

የኢትዮጵያ ህዝብ ያሸንፋል